# ሠ ቅ ዷ ሳ

የዐማራ ኅልውና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ልሣን

Amara Survival For Ethiopia's Unity Organization (ASEUO)



የዐማራ ኅልውና መጠበቅ፣ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነው!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!

ልዩ | ዕትም፳፰ | ቀን: መስከረም ፲፩ | በየ15ቱ ቀን ዘወትር ኀሙስ የሚወጣ


## የዴሞክራሲ መነሻ መሰረት ሕገመንግስት ነዉ!!

ላለፉት ፳፯ ረጅም ዓመታት የትህነግ/ኢሕአዴግ መድሎአዊና ፋሽስታዊ አስተዳደር በዐማራ ነገድ ላይ እየተፈፀመ ላለዉ የዘር ፍጅት፣ ማፈናቀል፣ መሬት ነጠቃና ማሳደድ መነሻ መሰረቱ በሻቢያ አጋፋሪነት ትህነግ(ወያኔ)ና ኦነግ ከኢትዮጵያ ሕዝብ በስተ ጀርባ ያዘጋጁት "የተሰኔ ስነድ" ተብሎ በሚታወቀዉና ዛሬም "የሕጎች ሁሉ ሕግ እየተባለ የሚዘመርለት ሕገመንግስት" ነዉና የዐማራ ኅልዉና ለኢትዮጵያ አንድነት ድርጅት (ዐኅኢአድ) ይህን መድሎአዊና የችግሮች ሁሉ ችግር ፈጣሪ ሰንድ በሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መንግድ ምንጊዜም በጽናት ይታገለዋል።

ሕዝብ በቀጥታ ባለተሳተፈበትና ባላጸደቀዉ ሕገመንግስት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ከቶዉንም አይታሰብምና የዴሞክራሲያዊ ሕገመንግስት አስፈላጊነት ጉዳይ በይደር የሚተዉ አይደለምና የትግል እንቅስቃሴአችን/ሂደታችሁን ሁሉ ወደዚሁ ትክክለኛ መንግድ የሚወስደን መሆኑን ማወቅ የግድ ተገቢ ነዉ። ለዚህ ደግሞ በእርግጥም ሁሉንም በቀጥታ የሚሳትፍና በሕዝብ አሰፋፍርና በዜግነት ላይ ለተመሰረት ሕገመንግሥት ዐኅኢአድ ይታገላል!!

ለዚህ ደግሞ ላለፉት ፳፯ ዓመታት በተለያዩ የሀገራችን ግዛቶች ለተከሰቱ ግድያዎችና ባለ ብዙ ፍርጃ የዘር/ጎሳ ጥቃቶችና ማፈናቀሎች ዋናዉ ምክንያት ሕገመንግስታዊና ሕገመንግስቱ መሆኑ በይፋ ታይቷልና ይህን አስቸጋሪ ሁኔታ ለመለወጥ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀጥታ የሚሳተፈበትና የሚያጸድቀዉ ሕገመንግስት ሊኖረዉ ይገባል ብሎ ዐኅኢአድ ያምናል። ከላይ ለማመላከት እንደተሞከረዉ ዐማራዉ ተወልዶ ባደገበት ቀዬዉና የአባቶቹ እርስቶቹ ተገፍቶና እንደ ወፍ ተባሮና ተገድሎ የሕግ ያለሽ እያልን ዛሬ ደግሞ ችግሩና ግድያዉ ተሰቦ ተሰቦ በሀገራችን መናገሻ መዲና አዲስ አበባ፣ ቡራዩና አካባቢ ነዋሪ በሆኑ ወገኖቻችን ላይ የተፈጸመዉን እጅግ በጣም ዘግናኝና አሳፋሪ ድርጊት መነሻ መሰረቱ ይሄዉ የሕጎች ሁሉ ሕግ የሚባለዉ የትህነግና ኦነግ ሕገመንግሥት የፈጠረዉ ችግር አይደለም ብሎ የሚከራከር ሰዉ/ድርጅት ምንስ አሳማኝ የመከራከሪያ ምክንያት ሊያቀርብ ይችላልና ነዉ "ሕገመንግስቱን መቀየር ይቅርና አንዲት ቃል እንኳ አትወጣም" እስከማለት ድረስ የተሄደ?

እርግጥ ነዉ ይህ የትህነግና ኦነግ ሕገመንግስት በዜጎች ላይ ያደረሰዉ የግፍ ጽዋ ሞልቶ በመፍሰሱ ምክንያት ሕዝባችን በሕዝባዊ አመጹን ቆርጦ በመግፋቱና በኢሕአዴግ ዉስጥ በተፈጠሩ የለዉጥ አራማጆች በወሰዱት ቆራጥና ሕዝባዊ ርምጃ በዉጭ የነበሩ/ርን ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ሀገር ቤት ገብተዉ/ን "በሰላማዊ መንገድ" አቋማችንን እንድናራምድ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይ አህመድና ቡድናቸዉ የወሰዱት ቆራጥና ታሪካዊ ርምጃ ዐኅኢአድም የዚሁ ዕድል ተጠቃሚ በመሆኑ

ከልብ እያደነቀ በፊት በሀገር ቤት በሕቡ ያደርግ የነበረዉን ድርጅታዊ ስራ እንሆ ዛሬ በሰላማዊ መንገድ በይፋ መስራት የቻለበት ሁኔታ ተፈጽሯል።

ይህም በመሆኑ በዚህ የሀገር ቤት ሰላማዊ ትግል ዐኅኢአድ ለሕዝብና በዐማራ ነገድ ዙሪያ ለተደራጁ ድርጅቶች ይዞት እየቀረበ ያለዉ ሀገራዊና ዋናዉና መሰረታዊዉ ድርጅታዊ አጀንዳ ችግር ፈጣሪዉና ዐማራን በማግለል መጀምሪያም በተሰኔ በሂደት ደግሞ የሽግግር ወቅትን ተንተርሶ የተቀረጸዉ የትህነግና ኦነግ ሕገመንግሥት (ሕገአራዊት) በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለሰፊ ዉይይት ቀርቦ የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀጥታ በሚያረቀዉና በሚያጸድቀዉ ዴሞክራሲያዊ ሕገመንግስት የመተካትን አስፈላጊነት በስፋት እየመከረበት ያለ መሆኑ ነዉ።

በሌላ በኩል ግን ከትህነግ ጋር በማበር በዐማራ ነገድ ላይ ከፍተኛና ዘግናኝ የዘር ፍጅት የፈጸመዉን ድርጅት እግር ተከቶ በአዲስና አስፈሪ አቀራረብ ከዉጭ እስከ ሀገር ቤት በስፋት እየቀሰቀሰ ያለዉ አክራሪዉ ቡድን መሪ ሲፈልግ ሀገራችን የምትመራዉ በራሱና በራሱ ቡድን እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ በተደጋጋሚ በአደባባይ ከመናገርና ከመስበክ አልፎ ተርፎ የትህነግና ኦነግ የተናጠል ሕገመንግሥት መሆኑን እያወቀና በየትህነግና ኦነግ ጉዳይ አስፈጻሚነት በወቅቱ በሊቀመንበርነት ተሰማርተዉ የነበሩት ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ ሳይቀር ሕገመንግስት ተብዮዉ ላይ ሕዝብ ያልመከረበት መሆኑን በይፋ የምስክርነት ቃላቸዉን መስጠጣቸዉ እየታወቀ ይሄዉ አክራሪ የኦነግ ጥንፈኛ ቡድን "ሕገመንግስቱ ለዉይይት ሊቀርብ ይቅርና አንዲት ቃል እንኳን አትቀየርም" ሲል ያሰቡት ቢሳካ ሀገራችንን ወደየት ሊወስዷት እንዳሰቡ አቋማቸዉ አሁንም , , , አሁንም በድጋሜ በግልጽ እየታየ ነዉና "ኧረ በሕግ አምላክ" ሊባሉ ይገባል!! ይባስ ብለዉም በቡራዩና አካባቢዉ የተፈጠረዉን አሳዛኝ ግድያና ማፈናቀል ወደየት ጠምዝዘዉ ለመስጠጋት እየሞከሩ እንድሆን በአግራሞት እያየን ነዉ!! ጅራፍ ራሱ ገርፎ ራሱ ይጮህ እንዲሉ!!

የሕገመንግስት ጉዳይ ሲነሳ ትህነግና ኦነግ የሰነዱ ብቸኛ ቀራጮችና ባለቤቶች ናቸዉና አቋማቸዉ ተመሳሳይ ከመሆኑ ባሻገር ሌላዉ ቀርቶ የአንድነት ኃይል የሚባለዉ ግንቦት ፯ት እንኳ ሳይቀር በሕገመንግስቱ ላይ መሰረታዊ ችግር እንደሌበት በተለያዩ መድረኮች በግልጽ የታየና የሚታወቅ በመሆኑ የኦነግ አክራሪ ቡድን ጣቱን የቀሰረ በግልጽና በአደባባይ ቋንቋ በዐኅኢአድ ና በዐማራ ነገድ ዙሪያ በተደራጁ አጋር ድርጅቶች ላይ ነዉና ዐኅኢአድ ፉከራዉንና እንግርግሪያዉን በቀላሉ የሚያየዉ አይደለም። እንግርግሪያዉ ከዚያዉ ከትህነግ የተለየ ባለመሆኑ ይህን መሰሉ ድንፋታ በዐማራ ነገድ ዙሪያ በተደራጁ ድርጅቶች ላይ ያነጣጠረ ከመሆን አልፎ ጠ/ሚ ዶ/ር አብይና ቡድናቸዉ የጀመሩትን መልካም የለዉጥ ጅምርና በሁላችንም ቀጥተኛ ተሳትፎና ርብርብ ዴሞክራሲያዊና ሉዐላዊነቷ የተጠበቀች ጠንካራ ሀገር ለመፍጠር በየአደባባዩ ላይ የሚነገረዉን ንግግር አደጋ ላይ የሚጥል ጭምር ነዉና ከወዲሁ አደብ ሊደረግበት ይገባል።

በተለያዩ የሀገራችን ግዛቶች የዐማራ ነገድ ተወልዶ ባደገበትና በአባቶቹ ርስት ትምክህተኛ፣ ነፍጠኛ፣ መጤ፣ ወራሪ የሚል ሕገመንግስታዊ ስያሜ ወጠለት በትህነግና ተላላኪ ካድሬዎቹ አማካኝነት (ዐማራ) ከቶዉን ያልተገደለበት፣ ያልተፈናቀለብትና ንብረቱን ያልተቀማበት አካባቢ እንደሌለ እየታወቀ ዐማራዉን በጅምላ ለመከራና ግድያ የዳረገዉን ሕገመንግስት አሁንም የኃይል አሰላለፋቸዉን ከትህነግ ጋር አድርገዉ በኃይልና በኃይል ሊጭኑብን በአደባባይ ይፎክራሉ። መሬት ነጠቃዉ፣ ግድያዉና ማፈናቀሉ የትህነግ ኦነግ ሕገመንግስት መገለጫ መሰረቶች ናቸዉና ዐኅኢአድ በሰላማዊ መንገድ ሁሉም የኢትዮጵያ ዜጎችን በእኩልነት ለሚታኙበትና ለሚዳኙበት ዴሞክራሲያዊ ሕገመንግሥት መታገሉን አጠንክሮ ይገፋል።

የአዲስ አበባ ነዋሪ የራሱን መስተዳድር የመምረጥና የመዘርጋት ተፈጥሮአዊ መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል ብለን በተለያዩ መድረኮች አቋማችንን ግልጽ ባደረግን መሬት ላይ ካለዉና ከእዉነተኛዉ ታሪክ አፈንግጠዉ በመዉጣት በዚያዉ በዉሸት የፈጠራ ትርክታቸዉ እኒሁ የትህነግና የኦነግ አዲስ ምልምሎች አዲስ ስም አዉጥተዉ ዐማራዉን "የምኒልክ ሰፋሪ" ማለት ጀምረዋል። ይህን ተከትሎ ግንቦት ፯ የኃይል አሰላለፉን ከወዲሁ ከነዚህ ኃይሎች ጋር ለማስተካከል ብሎ የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር አካል ዶ/ር ታደሰ ብሩ በትምህርት ብልጭታ መርሃግብሮ ስለ አዲስ አበባ ትንታኔ ሲሰጥ "ዐማራ መጤ" ነዉ እስከማለት ሄደ!! በመጨረሻም ይህ አደገኛ የሆነ የኃይል አሰላለፍ ገፍቶ ሂዶ በጥቁር ሕዝቦችና በዓለማችን ነፃነት ወዳድ ሀገሮች ዘንድ በነፃነት ተምሳሌትነትና የተጋድሎ ታሪክ በአንጸባራቂነቱ የሚታወቀዉን የሁላችንም ኢትዮጵያዊ አባቶች "የዓድዋ የድል ምልክት" የሆነዉን "የእምዬ ምኒልክን ሓዉልት" ለማፍረስ እስከመሞከር ድረስ ተሄደ!! የአፄ ምኒልክ ድል

የሁሉም ኢትዮጵያዊ ድል እንጅ የዐማራ አርበኞች ብቻ እንዳልሆነ ታሪክ አፍ አዉጥቶ ይናገራል!! በዚህም ረገድ እዉነቱን ዉሸት ብሎ ዐማራም የግሌ ነዉ ብሎ የቅጥፈት ትርግት ተናግሮ አያዉቅም።

አረንጓዴ፣ ቢጫና ቀዩ ቀለሞች የያዘዉ “ሰንደቅ-ዓላማም” ኢትዮጵያዉያን ለዘመናት ከጠላት ጋር ለነጻነታቸዉ የተዋደቁበትና የዚያዉ የዓድዋ ጦርነት የጋራ ድል ምልክት እንጅ የዐማራ ብቻ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም ነበር። በዚህ ረገድ ዐማራዉ የራሱን ሰንደቅዓላማ በሌሎች ላይ ለመጫን እንደሞከረ ተደርጎ መቅርቡ እጅግ በጣም የተሳሳተ ትርክት ነዉ። በዐኅኢአድ ጽኑ አቋም የዓድዋ ድል ሁሉም ኢትዮጵያዊ አባቶች በነቂስ ወጠዉ የተሳተፉበትና ክቡር ሕይወታቸዉን ቤዛ ያደረርጉበትና ዘመን የማይሽረዉ የጋር ድል ምልክታችን ከመሆኑ ባሻገር ኢትዮጵያም በዚያዉ መጠን የተለያዩ ማኅበረሰቦች የረጅም ጊዜ ታሪካዊ ቁርኝትና ትስስር ዉጤት ነች ብሎ ነዉና የሚያምን ዘመኑን የዋጀ የአብሮነትና የዴሞክራሲያ እኩልነትን መሰረት ያደረገ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓት ለመፍጠር እንታገል!!

**የዐማራ ኅልዉና መጠበቅ ለኢትዮጵያ አንድነት መጠበቅ ዋስትና ነዉ!!**